<u>ይደርስ ለሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው</u>

**<u>ጌታቸው ረዳ</u>**

<u>(ኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ)</u>



**<u>ፎቶ ጌታቸው ረዳ</u>**

በፌብሩዋሪ 2፣ 2018 ሳተናው በተባለ ድረገጽ የለጠፍከውን **<u>ወያኔያን የማንን ሀገር ነው እንገነጥላለን የሚሉት???</u>** በሚል ርዕስ በጻፍከው ርዕስ ውስጥ አጅግ ጸያፍ፤ነውራም፤ዘረኛ፤በታሪክ ያልተደገፈ የጥላቻ ፖለቲካ ስላስተላለፍክ፤ መልስ እሰጥሃለሁ።

ይህ መልስ ለሳተናው ተልኳል ቢያወጣው መልካም ካላወጣውም የትችት ነጻነት የሚያከብሩ በርካታ የድረገጽ ወገኖች ስላሉ በሕዝብ ይነበባል።

ካሁን በፊት ከብዙ አማታት በፊት እንዲህ ያለ ዕብደት የሚያስተጋባ ጽሑፍ በዘሐበሻ ድረገጽ በትነህ ነበር። በወቅቱ እኔም "ሰዓሊ ሆይ ስዕልዎን ያስተካክሉ" ብየ መልስ ሰጥቼህ ነበር። ዛሬም ያንኑ ዕብደት እንደ አዲስ መጣህበት።

አንድ ምሁር ወዳጄ <u>"ለስንቱን ዕብድ ብለህ መልስ ልተሰጥ ነው፤ ብርታቱን ይስጥህ</u>" ብለውኝ ነበር። ዕብድ እና ሞኝ የዘራው ንግግር ብዙ ዕብድ እና ሞኝ ሊያራባ መቻሉን ስለማውቅ የተቻለኝን ያህል እየደከምኩኝ ነኝ።

ይህም እውነት ነው። ካንተው ጋር የምስመማበት አንድ ቃል አለ። አንተ "<u>ምድረ ትግሬ</u>" የምትላቸው በዚህ እስማማለሁ። ምክንያቱም እዚህ ውጭ አገር የሚኖሩ ተቃዋሚ የሚባሉት <u>ምድረ ትግሬዎች</u> በኔ ላይ ካልሆነ (ውስጥ ለውስጥ የሚያጉረምርሙት ጥላሸት መቀባት) እንዳንተው ላሉ ትግሬን ከተፈጠሩበት ምድር

አውጥቶ አማራን ለመተካት የሚቀሰቅስን የታሪክ አምታች መልስ አይሰጡም። በኔ ላይ ሲሆን ግን *“ትግሬው በወያኔ ዘመን ተጠቃሚ ነው”* ስላልኩኝ አደባባይ ወጥተው ሃሳቤን ከመሞገት ይልቅ ውሃ ውስጥ ራሱን ቀብሮ እንደ እንደሚያጉረምርም *‘አዞ’* በቴሌኮንፈረነስ እንደሚያጉረመርሙ እሰማለሁ። ስለዚህም በሁለት ወገንተኞች ወገን የተጠመድኩ በመሆኔ ላንተ መልስ መስጠቱ እንዳፈረደብኝ እኔው ልጋፈጥህ እና መልሴን ይኼው። እነሱ ከቴሌ ኮንፈረንስ ጓዳቸው ወጥተው በግልጽ የትግራይን ሕዝብና ታሪክ ሊጋፈጡ የሞራል ብቃት የላቸውምና እኔ ልጋፈጥህ።

*መጀመሪያ ስለ ሳተነው/ዘሐበሻ/ ድረገጽ አዘጋጅ፡*

ሳተናው/ዘሐበሻ የተባለ ድረገጽ የሚከተለው ሕገ ወጥ ካርታ ማውጣት




አልነበረበትም። ምንጩ ያንተም ከሆነ፤ጭራሽ ማስወገድ ይጠበቅበት ነበር። ሆኖም እንዲህ ያለ ሕገ ወጥ ካርታ እየተለጠፈ “የወጠቶችን” ሕሊና በመበከል (ሳብቨርት) በማድረግ ልክ ተቃዋሚዎች የኤርትራኖቹን ሕገ ወጥ ካርታ እንደ አገር ተቀብለው “ኀማዳዋን ኢትዮጵያ” በማስቀመጥ በየድረገጾቻቸው እና በመጻሕፍት ሽፋን፤ከናቴራ፤ ቆብ፤ክራባት፤ በስብሰባ ማስታወቂያዎች፤በባዓላት፤በሙዚቃ ድግሶች ላይ ሕጋዊ በማድረግ ከፍተኛ የብረዛ ስራ በመስራት ላይ ናቸው። ለዚህ ነው በወያኔ የተሰጠው የሻዕቢያ “ሕገወጥ ካርታ” የተበከሉት “አብዛኛዎቹ” ተቃዋሚዎች “የባንዳ” ካርታ አክባሪዎች፤ በማለት የምኮንናቸው። ይኼው ዛሬ ደግሞ “የትግራይ ሪፑብሊክ” እያሉ ዕውቀት እያስተማሩ መስሎአቸው በድረገጾች ላይ “ትግራይ ሪፑብሊክ” ካርታ እና አገርነት በማጽደቅ ላይ ይገኛሉ። ፈረንጁም ታዳጊ ወጣቱም ሌላው ዓለምም ይህንን ሲመለከት ትግራይ አገር እየመሰለው ያጸድቀዋል <<የተመኛችሁት እንዳታገኙት ብዙም ባትጫኑን ጥሩ ነው>> ሲል አንድ ወያኔ በትግራይ ኦን ላይን ድረገጽ የጻፈውን አስታወሰኝ)። ወያኔ ሳያውጅ “የትግራይ ሪፑብሊክ ካርታ”

በማውጣት እየወተወታችሁ (ውትወታ ባያስፍልገውም) የተመኛችሁትን ተግባራዊ እንዳይሆን ጠንቀቅ ማለቱ ጥሩ ነው (ብጥብጡን ለማርገብ ማለት ነው!!)።

በነዚህ ነጥቦች እንነጋገር።

1- አንተ ትግራይ/አክሱም የአማራዎች እንጂ የትግሬዎች አይደለችም ትግሬዎች መጤዎች ናቸው። ብለሃል ለዚህም "የአክሱም ነገሥታት አማርኛ ስም ስለተላበሱም ሆነ ስለ አጼ ዮሐንስ አክሱማዊ/ትግራዊ ስላልሆኑ ወደ ጎንደር መሳብፈቅደዋል...ወዘተ ስትል ምንጭህ፣ኢ ከበላይ ግደይ መጽሐፍ እንደማስረጃ አቅርበሃል። እሳቸውም ቢሆኑ የአክሱምን ነገሥታት ሥራ እና ሥልጣኔ ጻፉ እንጂ /አክሱሞች/ (አማራዎች) እንጂ ትግሬዎች (አክሱሞች/ትግሬዎች) አይደሉም ወይንም ዮሐንስ ከፋሲል ዘር ሐረግ ይሳቡ እንጂ (ሁሉም ነገሥታት በጋብቻ ሲለሚሳሳቡ) የትግሬ/አክሱም/ ተወላጅ አይደሉም አላሉም።

ወደ ኋላ የምምለስበት ብሆንም ነገሥታቶቹ <u>ባንተ</u> አባባል <u>አምርኛ</u> ስም ስለያዙ ትግሬዎች አያደርጋቸውም። ይህ ከሆነማ ወደ ታች የማሳየው የጽዮን የትግራይ ርስት ጉልቶች የትግርኛ ስም ያላቸው መሆናቸውን እገልጻለሁ። ያም ቢሆን ነገሥታቱ እንኳን አማራ ወይንም ትግሬዎች ሊሆኑ ማወቅ ቀርቶ ነገዳቸው በድንጋይ ቀርጸው የተውሉን የጎሳዎቻቸውና የተዋጊ ሠራዊቶቻቸው ስሞች እንኳ እነማን መሆናቸውን ዛሬም ለይተን ማወቅ አልቻልንም። አመሐራ የሚል ሠራዊት ነበራቸው፤ ሐዳኒ የሚባል ተዋጊ ሠራዊትና ንጉሥም ነበራቸው። <u>አምሐራ</u> የሚለው በዛሬው አባባል <u>አማራ</u> ብንለው (ነፃ) የነጻነት ሠራዊት ብንለው፤ <u>ሐዳኒ</u> የሚለው ደግሞ <u>የትግርኛ</u> ቃል ስለሆነ <u>"እያባረረ የሚይዝ"</u> ማለት ነው አይደለም እንዴ? አንተም እንዳልከው ብዙ ነገሥታት እብራይስጥ ስም የግሪክ ስም (ዓረባዊ ስምም) አላቸው፡ ያ ከሆነ አክሱሞች ግሪኮች አይሁዶች ነበሩ ማለት ነው? እንዲያ ከሆነ የተሳሰተ ነው። ስለዚህ አማርኛ ስም ስለያዙ አክሱሞች/ትግሬዎች/ <u>የግድ</u> **<u>ብቸኛ ባለቤቶች</u>** ነበሩ ማለትም **<u>አያስኬድም</u>** ሕዝብ በነገሥታት ነገድ ሊጠራ አይችልም። አይጠራም። ንጉሡ የሌላ ነገድ ሆኖ አሕዛቦቹ የሌላ ነገዶች ሊሆኑ ይችላሉ። **<u>ንጉሥ ማለት "አዳም እና ሔዋን" ማለት አይደለም</u>**፡ አንድ ሰው ነው። አይደለም እንዴ? እንደ አሕዛቦቹ ከሌሎች መሰል የሌላ ትውለድ ነገድ በጋብቻ በስደት፤በገበያ ግንኙነት፤በጉርብትና... እንደሚጋቡ እና እንደሚዳቀሉ ሁሉ /እሱም/ነገሥታቶቹም (ከሌሎች አገር የነገሥታቶች ዘር ሳይቀር) ስለሚጋባ/ስለምትጋባ/ስለሚጋቡ ነገዳቸው ከአካባቢው ነገድ የተለየ

የሚሆንበት ወቅት አለ። ይህንን ቆይቼ እመለስበታለሁ። እንዳልኩት የትግሬም ስም ይያዙ አማራ ወይንም ግሪክ ወይንም አይሁድ ስም ይያዙ እንደ ዓዳምና እና ሔዋን ነገሥታቶች የሕዝቦች ወላጆች አይደሉም፤ መሪዎች/ገዢዎች እንጂ። ዮዲት እና ግራኝ አክሱምን ተቆጣጥረዋት ነበር ሃውልቱ ላይ ጽፈው እኔ የአክሱም ገዢ ነኝ ብለው ቢተውሉን ሶማሌዎች/አዳሎች/ "አክሱሞች" ትግሬዎች ' ነን ሊሉ ነው? ወይንም አገዎች (አገው ነበረች ስለምትባል (ሌሎች ግን አክሱማዊት አይሁድ ይሏታል፤እሱን ለጊዜው ላቆይ እና) መግዛትዋ እውን ነው። ግን ከላሊበላ/ከላስታ/ ወሎ የመጣች መሆንዋን ተረስቶ <<አክሱማዊት>> <<ትግሬ>> ነች ማለት ይቻላል። በስም አማርኛ የነበራቸው አክሱማዊያን ነገሥታት አክሱም/ትግሬ/ የአምሐራዎች ብቻ ነበረ ማለት ሊሆን ነው እንደዚያ ከተኬደ ማለት ነው!

2- ትግሬዎች እንጂ አማራዎች ባንዳዎች አይደሉም ብለሃል። እነዚህ እርባና ቢሶች እና መረጃ ቢሶች ስለሆኑ ይህን ለመመከት ብሞክር መጽሐፍ አይበቃም፤ ሰዎችንም ማስቀየም አልፈልግም። የድሮስ ተወው፤ የዛሬ ሆዳም አማራዎችስ ወያኔን ሰጥ ለበጥ ብለው ሲያገለግሉዋቸው እፊትህ ላይ ሆነው እያየሃቸው እንዴት ከሕሊናሕ ሊሰወሩብህ ቻሉ? ጠምንጃ እና ስንቅ እየተሸከመ ከተራራ ተራራ ከድምበር ድምበር እየተዋጋ ወያኔን ወደ መሃል አገር እንዲሻገር እየተታኮሰ 'ደግፎ አቅፎ' ወያኔን ያሻገረው ከትግሬዎች በተጨማሪ አማራዎች አልነበሩም? የመንግሥቱ ሃይለማርያም ንግግር እንኳ አታስተውስም። ያውም እኮ የትግሬ ገበሬ ባለው ሃይል ተደራጅቶ ሲያበቃ እንደ አንበሳ ወንበዴዎችን ሲከተክታቸው፡(ሲል መንግሥቱ የተናገሩት እናስታውሳለን። ይህ ደግሞ ሃቅ ነው።የወያኔው ብላታ ሃይለማርያም ረዳ ሳይቀሩ የሚሊሺያ ሃለፊ ሆነው ወያኔን ተዋግተው ነበር። ሌላው የትግራይ ገበሬ ወያኔን መድረሻ አሳጥቶአቸው ነበር ብዙ አመት እና በተለያዩ ገጠሮች፤ አንድ ምሳሌ ልስጥ- <<(የወያኔ ታጋዮች በአመንቲላ 'ገደል' ያለቁበት ታሪክ (ድድባ ደርጋዓጀን ገበሬ ያደረሰባቸው ጉዳት) ወያኔዎችም በራሳቸው ብዕር መዝግበውታል)።

ያ ሁሉ እንዳልነበረ ሆና ተገለባበጠ። ደርግ፤ ቀይ ሽብር ብሎ ባመጣው የጭፍጨፋ ጉድ ወጣቱ ፖለቲካ የነበረውም ያልነበረውም በጅምላ ሲያሰቃያቸው ኗሪው በርግጎ ወደ ወያኔ የኋላ፤ኋላ መሸሺያ ሲያጣ ተቀላቀለ እንጂ ፤ ወያኔን ታግሷል። ይህ ወያኔዎችም አይክዱትም።) መንግሥቱ ግን

እውነት ነው "እዚህ ሸዋ ዱሁር፤ሰላሌ፤ወሎ.....ገበሬው ምን እያለ ነው ወንበዴው ሲያሳልፈው የነበረ//? ሲሉ መንግሥቱ የተናገሩትን አስታውስ።

ስለዚህ ትግሬዎች ከጥንት ጀምረው ባንዳዎች ናቸው የሚለው ዝባዝንኬ ክስህ ላንድ ወገን ያንሻፈፈ <u>ወገንተኛ</u> ስለሆነ ቦታ አልሰጠሁትም። የኋላ ኋላ አትይ። መጀመሪያ ወያኔን የተዋጋ ትግሬ እንደነር አትርሳ። መንግሥቱ ምሁሩም፤ ያራሱ ካድሬዎችም፤ ከንቲባዎችም፤ ክፍለሃገር አስተዳዳሪዎችን ገበሬውም፤ ሠራተኛውም፤ ተማሪውም በወምበዴ ተባባሪነት እየጠረጠረ ሰብስቦ መቀሌ እና አዲስ አበባም እየወሰደ ወደ ማዕከላዊ አስገብቶ ትግሬ የተባለ እየገረፈ መረሸን ሲጀምር የትግሬ ከተሞች ባዶ ቀሩ። (ያመነም ያላመነም መጽሐፍ አንብብ)፤ ወያኔዎችን በቀጥታም በተዘዋዋሪም በባንዳነት ያገለገለው ማን እንደነበር መርምር።

በዚህ መጀመሪያ ጽሑፍህ ላይ የጠቀስከውን ጥቅስ ልጀምር፡

*<u><< ሰሞኑን እነ ወያኔ ለመልካም ነገር ሲጥሩ እንደቆዩ ሁሉ "…የማይሆን ከሆነ ምን ኢደከመን አንገነጠልም እንዴ!" ብለው ምድረ ትግሬን "ምን ይውጠናል? ምን እንበላለን፣ ምን እጠጣለን? እንዴት እንኖራለን?…!" አሰኝተው አሰደንግጠውታል፡፡>></u>* ብለሃል።

ያስቃል! ፈገግም ያስሰኛል። የኔ ወንድም እኔ ትግሬ ነኝ። እኔ እንደትግሬነቴ ወክየ ልንገርህ የትግራይ አክራሪ ሊሂቃን (አልትራ ኤትኒክ ናሺናሊስት) የመገንጠል ጥያቄ አስተጋቡ ሲባል ጥያቄው ፋሺስታዊ እና ሕጋዊ ከመሆኑ ሌላ "ትግራይ የትግሬዎች ብቻ አይደለችም"፤ "ኢትዮጵያዊ መሬት ነው"። የመገንጠል ጥያቄም የማይታሰብ ብዙ ህይወት የሚጠይቅ <u>"የመጨረሻ ዓለም ድምዳሜ የሚያመጣ ጦስ ነው"፤</u> ስለዚህም የማፍረስ መብት የላችሁም፡ ከሚል ክርክር እንጂ አንተ እንደምትቃዠው *<<""ምን ይውጠናል? ምን እንበላለን፣ ምንጠጣለን? እንዴት እንኖራለን?…!" አሰኝተው አሰደንግጠውታል፡፡>>* ከሚል ዝባዝንኬ ተራ ግምት አይደለም። እንዲህ ዓይነት ጅልነት መራቅ ይገባችኋል። ትግራይ አትገነጥልም እንጂ ብትገነጠል ሌላውስ አሁን እንዳለቺው "ኢትዮጵያ" ትኖራለች ብለህ ትገምታለህ? እውነቱን ልንገርህ፡- <u>ትግራይ በተገነጠለች በማግስቱ "ኢትዮጵያ ሕልውና ያከትማል!"</u>። እኔ <u>ያከትማል</u> የምለው ከከፋህም፤ <u>"ይገነጣጠላል"</u> ብለህ በለዘብተኛ ቃላትም ማስቀመጥ ከፈልገህ "ተጠቅመበት"።

እመነኝ፤ ትግሬ ከተገነጠለ፤ ሌላው ‘ማርና ወተት ቁርጥና ጠኝ እየተጎነጨ ተንደላቅቆ ይኖራል” የሚል ሕልም ካለሕ ወደ ጤናማ ሕሊናሕ ተመለስ። ትግሬ ሌሎቹ ከመገጣጠማቸው በፊት ኖረዋል፤ ዛሬም ለወደፊቱም ይኖራሉ። እመነኝ! **ትግሬ ከከፋው ሁሉም ይከፋዋል፤ ሌለው ከደላው ትግሬም የማይደላው ምንም ምክንያት የለም።** ወገኖቼ ከቅዠትና ስሜት ውጡ! እኔ በሁለቱ ወገን ላሉ ጠባብ አማራዎች እና ትግሬዎች እኩል እቃወማቸዋለሁ። ከፋን የምትሉ ምድረ ጠባብ ትግሬና እና ምድረ ጠባብ አማራ እየተመኛችሁት ነውና ይክፍችሁ። እኛን አይጨምረን እንጂ እናንተን ብቻ ይዞ የሚሄድ ኩፋኝ (በደዶ/ፈንጣጣ) ካለ ይስጣችሁ !

እንዲህም ትላልህ፡-

*<<…በርካታ የዋህ ሰዎች እንደው በተገላገልን! በሄዱልን!...,ይላሉ እነ ወያኔ ይሄንን (የመገንጠል) ነገር ለቀልድ ያህል ወይም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስደንገጥ ያህል ብቻ የተናገሩት መስሏቸዋል፡፡ እውነቱ ግን ቀልድም አይደለም ለማስደንገጥም አይደለም፡፡>>*

እዚህ ላይ እውነት ብለሃል። ለማስደንገጥ ያህል የተናገሩት አይደለም። በዚህ በአዲሱ መጽሐፌ ወደ ሃያ ሁለት ገጽ ያህል ያስፈርኩት ሰነድ (ማንኛችሁንም ያላገኛችሁት ከ10 አመት በፊት የተሰራጨ ቅጽ “ፎርም” የተሞላ ኢመይል ሰነድ) የተደራጀ ቡድን አለ። እነ ሙሉወርቅ እና እነ ገብረኪዳን ደስታ፤ ሰለሞን ዑንቋይ --ከኤርትራ ደግሞ ለምሳሌ ልጥቀስ “ዶ/ር ፍስሃጽዮን መንግሥቱ” (የመድህን አባል የነበረ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር- የአያቶቹ የአከለጉዛይ “ትግራይ ትግርኚን” አጀንዳ አስፈጻሚ የሆነው) አለ። እነዚህ ከ10 አመት በፊት ያሰራጩት **<<“ማሕበር ሰላምን ሕውነትን ትግርኛ ስድራቤታትን ተዳወብቲ ብሄራትን”>>** **<<የትግርኛ ተናጋሪ ቤተሰቦች የሰላምና የወንድማማችነት ምስረታ>>** የሚለው ድብቅ አጀንዳ ያንን ማንበብ ነው። ስለዚህም ለማስደንገጥ አይደለም። እነሱ አይደነግጡም -ሲሰሩበት የቆዩ አጀንዳ ነው። መደንገጥ ያለብህ እኔ እና አንተ መሆን አለብን።ምክንያቱም አገራችን እንደገና ወደ ሩዋንዳ እንዳያሸጋግርዋት መደንገጥ አለብን። በዚህ የማይደነግጥ ሰው ካለ “በድን” ነው ማለት ነው።

## ለግንጠላው መነሻ ምንድነው ለሚለው ስትመልስ

(ሀ) *<<ይህ የመገንጠል አማራጭ ወያኔ ከተጠያቂነት ማምለጫ አድርጎ የሚያስበው ብቸኛው መንገዱ ነው፡፡>>* ብለሃል።

አንዱ ምክንያት አዎ ያ ሊሆን ይችላል። አይሆንም ልል አልችልም (ከሠሩዋቸው ወንጀሎች ሲታይ)። ዋናው ምክንያት ግን ያ አይደለም። ምክንያቱም "ይህ የታጠቀ መንግሥት/ቡድን" ነው። ቢያንስ ወንጀሉን በሙሉ የሚጠርግለት ድርድር (ከሕብረተሰቡ ፍላጎት አንጻር "ይውረዱልን ብቻ" ከሚሉ እና ተቃዋሚውም ከመፋጠጡና አገር ከሚበጠበጥ ይቅርታ ተደርጎላቸው ቢወርዱ እንስማማለን" ምሊሉ ተቃዋሚዎች እንዳሉ ከቁም ነገር በማስገባት) ይህን እና የመሳሰሉ እውን የማድረግ ዕድል የሚችልበት አቅም ስላለው "ከተጠያቂነት ለመሸሽ ነው ግንጠላን ያቀደው" የሚለው ከነጥቦቹ አንዱ እንጂ ግምባር ቀደም ነጥብ ምክንያት አይደለም። ሲከፋው "የድርደሩ ነጥብ በፈረንጆች በኩል የሚያቀርበው ይህ የወንጅል ይቅርታ/ተጠያቂነት የሚሰርዝ ድርድር እንደሚቀርብ አልጠራጠርም። ተቃዋሚውም ወያኔ እንዲወርድ ስለሚቋምጥ ያንን ተሎ ይስማማል። ባይሆን ተቃዋሚው እራሱ ወደ ድርድሩ ያመጣው ይሆናል።" በዚህ ጉዳይ እኔን አስታውሱኝ! ምን ብሎ ነበር በሉኝ። ምክንያቶቹ ካንተ ለየት ያለ ልግለጽ።- (ልምድ ያካበቱ የቆዩት የድሮ 'ቬተራን' መሪዎች በሞት አንድ ባንድ ካልተመናመኑ በቀር- የጠቀስከው "ፍርሃት" ቀዳሚ አጀንዳቸው ሊሆን አይችልም።

ለግንጠላው መነሻዎቹ፤

1) በረዢም ጉዞ የተጓዘበት አማራን የመጥላት ሁኔታ ህዋሳቱ ኢትዮጵያ የምትባል የአማራ/የምንልክ/ሃይስላሴ/መንግሥቱ አድርጎ ስለወሰዳት፤ ያንን አገር በጤና መተው ከፖለቲካ አጀንዳው ሲታይ የማፍረስ አጀንዳው አንዱ ይህ ሲሆን (አስታውሱ ከአማራዎች ጋር መኖር አይቻልም፤ ሕብረተሰባዊ ጤንትም አታገኝም የሚለውን ከመጀመሪያ ማኒፌስቶውን አስታውሱ)፤
2) ወደ መንግሥት ከመምጣቱ በፊትና በወንጀል/በንቅዘት ከመበላሸቱ በፊት በረሃ እያለ ከመጀመሪያ ጀምሮ የነደፈው 'የትግራይ ረፑብሊክ' የመገንባት ዓላማው እውን ለማድረግ። እውን ለማድረግም አንቀጽ 39 ቀርጾ የመገንጠል መብቱን ተጠቅሞ ለመሄድ አስፍሯል። ሊያስወግደው ያልፈቀደበትም ምክንያትም ሆነ የድርጅቱ የመታገያ ስሙ እስካሁን ያልቀየረበት ምክንያትም ያ ዓላማ እንዳለ ነው፡

3) ኢትዮጵያን ለማበጣበጥ በውጭ ሃይላት የተጠና በዚህ ድርጅት እና በመሰል ገንጣይ ቡድኖች ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ሥልጣን እንደመጣ አንተም ሆነ ሌሎቻችሁ እንደማትስቱት እርግጠኛ ነኝ። የወዳጄን ስም አደጋ ላይ ላለመጣል ስል ሁለንታዎቹን ሳልጠቅሰ በደፈናው አልፈዋለሁ፡ ኢትዮጵያን “አማራን” ማዕከላዊ ጠላት አድርጎ በማስተማር በነገድ እና በተለያዩ ባንዴራዎች አስታክኮ የማፍረስ ምስጢሩን በእንግሊዝ አገር (መሲያኒኮች) ተጠንቶ ለምልመላ ከተወሰዱ ወዳጆቼ አንዱ የሚያስፈራ ታሪክ ነግሮኛል። ፍረጡ፤ውረዱ፤ውጡ ሃቁ ይህ ነው። ኢት ኢትዮጵያ በወያኔዎች ብቻ የተደረገ የማፍረስ ሴራ አይደለም። የውጭ ትብብር፤ጥናት እና ግፊት አለበት። የኦነጎች ባንዴራ ሳይቀር እዛው አስፈሪው አዳራሽ ውስጥ አለ!! ለዚህ ዕቅድ የታጩና ትግል ላይ ያሉ በዓለም ዙርያ ያሉ “ሽምጥ ተዋጊዎች” ባንዴራዎች ሁሉ አዳራሹ ላይ ተደርድረው ይታያሉ።እያስደነገጥኳችሁ መሁኔን ይገባኛል። ሃቁ ግን ያ ነው። አምየ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ ፈጣሪ ካልዘረጋች ሃቁ ይህ ነው! እንኳን እኛ እላይ ያሉ ከጥቂቱ በቀር ሁሉም ሃላፊዎችም ሆኑ ተራ የወያኔ አጎብዳጆች ምስጡረን አያውቁትም።

እናንተስ ስታስቡት እንዲህ ያለ ግፍ፤ዕሪታና ዋይታ እና ብሔራዊ ወንጀል፤ የባሕር ዕገዳ፤የተለያዩ የጎሳ ባንዴራዎች በጥንታዊት አገር ሲፈጸም መንግሥታት ዝም ብለው ሲያዩ ምን ያሳያችኋል? ወንጀል ሰርተው ወደ አውሮጳ እና አሜሪካ ያለ ምንም እገዳ ሲኖሩ፤ሲመላለሱ የሚፈቅደው ማን ነው? ሕዝብ ሲገድሉ የነበሩ አሜሪካ እና አውሮጳ ሲገቡ ምን አይነት ቃለ መጠይቅ እና ኑዛዜ እያደረጉ እንደገቡ የምናውቀው ነገር የለም። ሕዝብ ያልተነገሩ የተደበቁ ብዙ ምስጦሮች አሉ ግን አሁን ቦታው አይደለም። ብዙ ወንጀል የሠሩ ከሃዲዎች በየዓለማቱ እና እኛም ጋር እዚህ ቁጭ ብለው ግማሾቹ በታቃወሚ ስም አሉ፤ አንዳንዶችም አፋቸው ዘግው ተቀምጠዋል። ለአገሬ ሕዝብ ግን አልቅሻለሁ። አገሬ በሰላም እንድትኖር እመኛለሁ። ለዚህም ነው እየቆጨኝ ዕረፍት ያጣሁት። ሌሎቹ ቁጫኞችስ ተውዋቸው እናንተ የምታውቅዋቸው እነ ታምራት ላይኔ ተንደላቅቀው አሜሪካ አገር እንዲኖሩ ሃይማኖት ሰባኪዎች እንዲሆኑ የፈቀደላቸው ማን ይሆን? ተከድኖ ይብሰል!

4) ትግራይ ትግርኚን የመመስረት አላማ እና ኢትዮጵያን ለም መሬቶች ወደ ትግራይ የተጨመሩበት እና ከሱዳኖች ጋር ወዳጅነት የተፈጠረበት ምክንያትም ሆነ፤ ጸረ አማራ ከሆነው አማራዎችን መጨፍጨፍ እና በማባረር እየዛተ በቴፕ ሪኮርድና በቪድዮ የተቀዳው የኦጋዴኖቹ ሶማሌዎቹ መሪ የሆነው "አብዲ" ጋር የጠበቀ ግንኙት የማድረጉ ሁኔታም) ኢትዮጵያን ለማፍረስ እንዳነጣጠረ ግልጽ ስዕል ይሰጣችኋል። አደልም እንዴ?

5) ስለዚህ ከወንጀል ለመሸሽ ሲል ነው ትግራይን ለመገንጠል ያቀዱት የሚለው፤ የመጨረሻው ነጥብ ብቻ እንጂ የመጀመሪያ ቀዳሚ ምክንያት አይደለም።ይሄ የፓልቶክ ፖለቲካ ግምት ነው።

እንዲህም ብለሃል፡-

<u>*(ለ)<< ሲገነጠልም ከተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል አይደለም የሚገነጠለው፡፡ እንደዚህ የሚመስላቸው በርካታ የዋህን ወገኖች አሉ፡፡ ከዚህ የተሳሳተ አስተሳሰባቸውም ተነሥተው "ውይ ምነው እንዲያው በተገነጠሉና በገላገሉን!" ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ እንደዚያ አይደለም ወያኔ የሚያደርገው፡፡ ወያኔ ለመገንጠል የሚያስበው ኢትዮጵያን አፈራርሶ ነው፡፡ ቀሪዋን ኢትዮጵያን እንዳለች ትቶ ቢገነጠል ምን እንደሚከተለው ጠንቅቆ ያውቃልና፡፡>>*</u>

ይህ አባባል ልክ ነህ። ግን ቀሪዋን ኢትዮጵያ እንዳለች ተዋትም አልተዋትም፤ ወያኔ ከተገነጠለ በኋላ ቀሪዋን የማቆየት አለማቆየት ደንታው አይሆንም። ምክንያቱም ትግራይ ወዲያውኑ ስትገነጠል- ጋሻ ጃግሬዎቹ <u>"ኦነጎች፤ሶማሌዎች፤ሲዳማዎች.....ብዙ ብዙ ከወያኔ የባሱ ያበዱ ተገንጣዮች ስላሉ>></u> በማግስቱ የተሰጣቸውን ድምበር አጥረው ሰውን ማባረር ይጀምራሉ። ለዚህ ነው የግንጠላ ስራ የምንቃወመው። እንዲህ ሲሆን "የሩዋንዳ" ታሪክ በከፋ መልኩ ይደገማል ማለት ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ አስቀድሞ እንድትፈርስ በክልልና በባንዴራ አጥሮ ያስተዳደራትም መነሻው ይህ ነው። የውጭ ሃይላት ጥናትና ፍላጎትም ያ ነው። የደቡብ ሱዳንን ታሪክ አስታውሱ! አል-በሽር በአሜሪካኖች ግፊት ከተከሰሰበት ከክሱ ነጻ እንዲሆን ደቡብ ሱዳንን ነጻ እንድትሆን ፈቀደላቸው፤ ገሃነም ውስጥ ገብታ ሕዝቦችዋ እርስ በርስዋ "በነገድ" የጥላቻ

እየተዋጉ የጅብ እራት ሆነው “ሕዘብኦችዋ እርይ የረዳት ያለህ ይላሉ”። አሁን ፈረንጆች ያቀዱት እልቂት እየተፈጸመ ነው።

ቀስ ብሎ በተራ የተቀረቺው ሱዳንም፤ በምስራቃዊ ሱዳን በቤጃ ብሔዋሪ ንቅናቄ ከዚያም በዳርፎር ከዚያም በጐንቶች ወዘተ.....ተከፋፍላ የተቀረቺው ሱዳንም “ነበር” ተብላ ትጠራለች። አሁን ያለው የድምብር ማጠር ከባባ ታዘቡልኝ። የዓረቦች አገሮች ሕልፈተ ሞት “እየተገባደደ” ነው- እስላምና ኣረብ አገሮች ሶረያ፤ ሶማሌ፤ኢራቅ፤ሊቢያ....) አፈር ድቤ ሀነዋል።

ኤርትራም ነጻ ተብሎ በሻጥር ተገነጠለች፡ <<ሕዝቦችዋ በጦርነት እና በስደት እየለቀቁ ባዶ ቀርታለች። ጥቂቶቹ ይፈነጩባታል፤ ሕዝቧ ግን በጣረ ሞት ያቃስታል። ኢሳያስ በሕመምም አደጋም፤ በግድያም ሲወገድ ቆላማ እና ደጋማ (ትግራይ ትግርኚ) ትግል ይገጥማል። ወያኔ ይገባበታል (ትግራይ ትግርኚን ለማሳካት) ኩናማ፤ዐፋር የብሔር ጥያቄ እስከ መገንጠል (አሁን የያዙት አጀንዳ) በመጠይቅ ክርክር ውስጥ ይገባሉ። ካልሆነ ወደፊ ትግራይ አንቀላቀላላን በማለት ኤርትራኖችን በማስፈራራት “ፍልስልሱ” ይወጣል። ቆላማ ዎቹም ዓረብኛ ቋንቋ በትግርኛ ስለተረገጠ ወደ ሱዳን እንኄዳለን ብለው ሃረንደዋ እና ብሌኖቹ አሻፈረኝ ይላሉ። ሓመሴን ሰራየ አከለጉዛይ ከትግራይ ጋር አዶሊስን ምጽዋን ( አሰብን) ይዞ ለመኖር ስምምነት ለመፍጠር ሊንደፋደፍ ነው። ኤርትራም “በነበር” ተብላ ትጠራለች/ ብሔረ አጋአዚ/ትግራይ ትግርኚ” ትባላለች።

ኢትዮጵያም ‘ወደብ አጥታለች፤ በጎሳ ተከፋፍላለች፤ ኤርትራ አጥታለች፤ ቀስ ብሎ ትግሬም ፤አሮሞም፤ ሶማሌውም..... የተመኘውና የተዘጋጀለትን የመጥበሻ ምድጃ እራሱን በመከተት እራሱን ወደ ማጥፋት ወጥመድ እያመራ ነው። የዋን ወርልድ-አርደር አጀንዳም በዚህ የገባደዳል።

አማራውን ነፍጠኛ በማለት የሚጠራው ዶ/ር መረራ ጉዲና እንኳ በቅርቡ አታዩትም? አሮሞዎች ከብትና በግ እያረዱ እየሸለሙ በእልልታ ሲቀበሉት፤የተውለበለበው ባንዴራና ኣናቱ ላይ ያጠለቁለት ባሕላዊ የማዕረግ (ዘውድ) እና ካባ አታዩም? ምንን ታዘባችሁ? “በኢትዮጵያ ሰንደቃላማ ‘ሓር’ የተጠለፈ የጀግንነት ጎፈር” ሳይሆን “ወያኔ እና ኦነግ ለአሮሞዎች የፈቀዱላቸው/ የሰሩላቸው/ ዓረባዊው ቀይ፤ነጭ እና ጥቁር ሓር የተጠለፈው ባንዴራ ምልክት” ነበር ያጠለቁለት።

ስለሆነም፤ ወያኔ በተገነጠለ ማግስት እነ መረራ፤ እነ በቀለ ገርባ እነ ሌንጮ .... 3/4ኛ የኢትዮጵያ መሬታቸውን ይዘው ኦሮሚያ ወደ እምትባለዋ የማርና የወተት ቅቤ ወደ እሚፈስባት ክርስትያኖች እና እስላሞች ተቃቅፈው ተጋብተው ወደ እሚኖሩባት! በነ ጃዋር ፊታውራሪነት ወደ "ኦሮሚያ ሩፑብሊክ" በመግባት "አማራውን ትግሬውን፤ጉራጌውን፤ሶማሌውን...ወዘተ" በሜጫ አንገቱን እየቀነጠሱ ማባረር ይጀምራሉ ማለት ነው።

በሕልም ገነት ውስጥ እየደነሰች ያለቺው 'አዲስ አበባ' የማን ውሽማ/የማን ሚስት ናት? የሚለው ትግል ያኔ በመተላለቅ ይለይላታል ማለት ነው። ያኔ ሰዓሊ አምሳሉ በየትኛው ወገን ተሰልፈህ ማንን እንደምትረግም ላንተው ልተወው። ወይንም ትግሬ መጤ ነው፤ ትግሬ መውጣት አለበት 'አማራው የትግራይ ባለቤት ነው" ወዳልከው ቦታ በመምጣት የቅድሚያ ውግያ ትከፍታለህ ወይንም አዲስ አበባን ለማስከበር ስትል የምታደርገው ሸዋ ውስጥ የፍልሚያ ቅድሚያ "ትስጥ፤አትስጥ" ለማን እንደምታስቀድም አንተ እወቀው። ቀሪው ታሪክ ነው! ከዚያ ይሰውረን ብቻ!!!

እንዲህም ብለሃል፡-

*<< አንዱ ወያኔ ይሄን የመገንጠል ነገር ነጻ ጋዜጠኛ ነኝ ለሚል የወያኔ ሰላይ የማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛ ሹክ ማለቱን ተከትሎ በርካቶች "እንዴ! እንዴት? ትግራይ እኮ የኢትዮጵያ መሠረት ነች! ፣ የኢትዮጵያ መሠረት ከሆነ ሕዝብ እንዴት እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ይወጣል? የአክሱም ሥርዎ መንግሥት፣ ቅዱስ ያሬድ፣ አክሱም ጽዮን....!" ምንትስ ምንትስ እያሉ ለማግባባት ሲጥሩ ተስተውለዋል፡፡*

*ይሄ ነገር ማለቴ ትግሬን የአክሱም ሥርዎ መንግሥት ባለቤት አድርጎ የመሣሉ ነገር ባለማወቅ በሚፈጸም ስሕተትና በማወቅ በሚፈጸም ስሕተት በሁለቱ ምክንያቶች የሚነገር ቃል ነው፡፡ 1ኛ. ትግሮች አሁን ላይ በአካባቢው መገኘታቸው ጠልቀው መመርመር በማይችሉ ወገኖች በፈጠረው የተሳሳተ ግምት 2ኛ. ከጥንት ጀምሮ ባዕዳን ሀገራችንን ለመውረር በመጡ ቁጥር ከዐፄ ሠርፀድንግል ዘመን ጀምሮ ትግሮች በባንዳነት ለባዕዳን እየተሰለፉ ሀገራችንን፣ ሕዝቧንና መንግሥቷን በተደጋጋሚ እየወጉ ስለሚያስቸግሩ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲሰማቸው በማድረግ ከዚህ የጥፋት ተግባራቸው እንዲታቀቡ ለማድረግ ታስቦ ለፖለቲካዊ ጥቅም ሲባል ነው፡፡*

*በእነዚህ ሁለት ምክንያቶች አክሱም የትግሬ እንደሆነ ተደርጎ የሚነገረው ነገር እያደር እውነት እየመሰለ መጥቶ ዛሬ ላይ ሁሉም እንደ እውነት የሚያወራው ነገር ሆኖ ቁጭ ብሏል። ነገር ግን ትግሮች የአክሱም ሥርዎ መንግሥት ባለቤት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አንድም እንኳ ቁሳዊም ሆነ ትውፊታዊ ማስረጃ ተገኝቶ አያውቅም። ማስረጃዎችና ትውፊት የሚያረጋግጡት አክሱም የአማራ መሆኑን ነው።*>>

ስትል በሚያስቅ በሚያናድድም ሁኔታ ለአክሱም ትግሬዎች ምናቸው አይደለም፤ ዋናው ባለቤቱ አማራ ነው ስትል ትንሽ ያለ ሰቀቀን ጀሮን በሰለማዉያን ጀሮ የሚሰቀጥጥ 'ጅራፍ' ታጮሃለህ። ሁለቱም ያንድ ዘሮች ናቸው ብትል ያምርብህ ነበር። ናቸውም! አክሱም/ትግሬ/ ለትግሬውም ለአማራውም ለሌሎቹም እኩል ይደርሳቸዋል ብትል ጨዋነት እና አዋቂነት ነበር። ግን መለስ ዜናዊ በድንቁርናው እና በጠባብነቱ አክሱም ለወላይታው ምኑ ነው? እንዳለው ሁሉ አንተም 'አክሱም' 'ለአማራው' እንጂ 'ለትግሬው' ምኑ ነው?" ስትል፤ የመለስ ዜናዊ "ጅልነት" እየታለበስከ ነው። ጅልነት ብቻ ሳይሆን ከንቱ ትምክሕትና መፈራገጥ !

አንተ ምንትስ ምንት የምትለው የአክሱማውያን ሕሊና እና ብርታት ማናናቁ ባንተ አልተጀመረም፤ ተማሩ የሚባሉ የቅርብ ወዳጆቼም ይህን ግብዝነት ሲያስተጋቡ ሰምቻለሁ። ወያኔን መጥላት አክሱምን ማንኳሰስ ማለት ትንሽ ያለማደግ ነው።

ሌላው ትግሬዎች በባንዳነት ትከሳለህ። አማራዎች በባንዳነት ያልተከሰሱበት ታሪክ ብትንግረን እንቀበልሃለን።ግን ያንን ለማድረግ በቂ ችሎታ የለህም። ሁለቱም መልሶቼን ልስጥህ።

ትግሬዎች በ7ኘው ክፍለዘመን የመጡ ቤጃዎች ናቸው፡ የሚሉ የታሪክ ምሁራን የሆኑ ወዳጆቼ አሉኝ። እኔም በዚህ ሁኔታ ለማጣራት ትግል ገጥሞች ያልገለበጥኩት መረጃ የለም። ሁሉም ሙሉ በሙሉ ሊያሳምነኝ አልቻለም። ያሳመኝ ነገር ቤጃዎች (ሃረንድዋ) የአክሱምን ስርወመንግሥት ማፍረሳቸው ከመነገሩ ሌላ የአካባቢው ስም ትግረ ከጊዜ ብዛት (ትግረኛ/ትግራይ/ትግራዋይ..) ብለው መሰየማቸውን ተቀባይነት አለው። የስም መቀያየር ሁሉም ለየቅሉ ይተረጉመዋል። አክሱም "ቁልዚ" ስትባል ነበር፡ ኢትዮጵያም ስትባል ነበር ፤ኗሪዎችዋም "በለው" ይባሉ እንደነበር ይገልጻሉ። አክሱም ማለት አገውኛ ነው የሚሉ አሉ። አክሱም የሚለው ትርጉም ዓረብኛ ነው የሚሉ አሉ (ደብተራ ፍስሓ

አብየዝጊ)፤ ግሪክ ነው የሚሉ አሉ (አኩዓሱም) ግሪክኛው አጉዋ "ዉሃ" ነው ሱም "ሹም" ማለት ነው የውሃ/የባሕር ሰም ማለት ነው ይላሉ። ሁሉም እንደ ሚመቸው፤ፋደል እያቀራረበ እየተረጎመው ነው።

## *መልሴ እንደሚከተለው ነው።*

ሁለቱም ያንድ ስርወ ነገድ ወገኖች መሆናቸው የማምን ብሆንም፡ ሆኖም አማራዎች ግን አንድም ከዚህ ቀጥሎ በምገልጸው ዘመን የትግራይ /አክሱም/ትግራይ/ ኗሪዎች መኖራቸውን የሚናገር ሠነድ አላየሁም (አማርኛ ጽሑፍ መኖሩን ግን ጠቅሻለሁ) አማርኛ ቃላት መኖሩን እና አምሐራ በተባለ ስም የተጠራ ሠራዊት እንደነበረም አውቃለሁ። ግን ትግሬዎች ባላባቶች አይደለም ማለት አይደለም። ስለ ትግሬዎች ታሪክ ከጥንት ጀምሮ ባለባትነት እና እዛው መኖራቸውን ግን ባጭሩ ላስረዳ።

አንተም ሆንክ እኔ በብራና እና በድንጋይ ላይ የሠፈሩ ጽሑፎች ብዙ የዕውቀት ክምችት የያዙ መሆናቸውን እናውቃለን። በተለያዩ ቦታዎች በልሽት ሳይገጥማቸው የሚገኙ አስደናቂ ቤ ክርሰትያናት ፤ቤተ መነግሥቶች ውስጥ የተቀመጡ የግዕዝ መጻሕፍት ባዷቸውን አይደሉም።የጸሐይን፤ የጨረቃ ምህዋርን፤የግብር አሰባሰብን የዝናብ ጉዞና ትንተና፤የነገሥታት ገድል፤ የአሕዛብ አሰፋፈር፤ነገዶች ስም፤የቦታ ስያሜ፤ጦርነቶችን ወዘተ.....የሚያብራሩ ናቸው። ከነዚህ መጽሐፈትና ሃውልት ላይ የተጻፉት መካካል ትግሬዎች በ7ኛው ክፍለዘመን ሳይሆን ገና ነገሥታቱ አብርሃ እና አጽብሃ ሳይወለዱ የነበሩና እነሱም በነቡረበት ዘመን የነበሩ መሆናቸውን ከነገሥታቱ ጋር አብረው የነበሩት ሊቃወንት እና ዘጋቢያን የተውልንን የግዕዝ ሰነድ ልጥቀስ እና የአምሐራ ሕዝብ (ሰብዓ አምሐራ) በዚህ ውስጥም ሆነ በሌሎች መጽሐፍቶች የተጠቀሱበት ካለ ወይንም በሌሎች በዘመነ አክሱም ነበሩ የምትላቸውም ካሉ ማስረጃ እሻለሁ።

በትግሬዎች የተጻፈ ነው እንዳትለኝ ሌላውን ትቼ በሊቀ ሊቃውንቱ አማራው (ጎጃሜ የመስሉኛል) አስረስ የኔ ሰው <u>ትቤ አክሱም መኑ አንተ?</u> (አክሱም አንተን ማን ትልሃለች? ማለት ነው በግረድፉ እኔ ስተረጉመው) አብርሃ አጽብሃ የተባሉ ነገሥታት ከአክሱም ጀምሮ መላዋን ትግሬ እየተዘዋወሩ እንዲሁም በሸዋ እስከ ጎጃም እና ሌሎች ቦታዎች ቤተ መቅደሶችን (ቤተክርስትያናትን) ስያንጹ፤የተውትን ሰነድ እንዲህ የነበባል።

<<“ወገብሩ ትእይንተ በምድረ አይባ ወሐነጹ መቅደሰ ባህየ ታሕተ እግረ ደብር ዘትሰመይ ጉልሳ። ወኃለፉ እምህየ ወበጽሑ ምድረ ሐረማት ወሐነጹ በህየ አሐተ መቅደስ ዘትሰመይ ሐውዜን ወእንዘ ሀለው በህየ ሰብዓ ትግሬ ወይቤልዎሙ አብርሃ ወአጽብሐ ለካህናተ አክሡም መጽአ ጸላዒ እምአመ ሖርነ ወይቤሉ ካህናት እወ ይመጽእ ወየሐው ከነ በከዊነ ኲሉ።ወእምድኅረዝ ሖሩ መካነ አክሡም ወዓቀሙ በህየ ሐውልተ በአምሳለ ትእምርተ መስቀል ከመ ኢይቅርቡ ሰይጣናት ወኃለፉ እምህየ ወገብሩ ትዕይንተ በምድረ ጽራዕ ወሐነጹ መቅደሰ ኀበ ጽንፈ ባሕር ዘትሰመይ ውቅሮ ወእሐተ መቅደስ ሐነጹ በመደቁ ዘሡናይ አር አርዓያሃ ወአልቦ ዘይትማሰላ እምኩሉ መቅደሰ ዘተኃንጻ ቀዳሚ ወተሠወረት። በምድረ አጽሊ ....” (ገጽ 204 አስረስ የኔ ሰው ትቤ አክሱም መኑ አንተ )>>

<u>ወደ አማርኛ ትርጉም</u>

ምድረ አይባ ላይ ሰፈሩ። የባህ መቅደስን (= ቤተ ክርስቲያን) ከእግር በታች ሠሩ። እዚያ ሐውዜን የምትባል መቅደስ (= ቤተ ክርስቲያን) ሠሩ። <u>የትግሬ ሰዎች እዚያ እያሉ</u> አብርሃና አጽብሐ የአክሱም ካህናትን እንዲህ አሏቸው፤ “ከሄድን ጀምሮ ጠላት መጥቷልን?” ከህናቱ፤ “አዎን፤ በሆነው ሁሉ ሆኖ ይመጣል ይሄዳል።” ከዚያ ወደ አክሱም ቦታ ሄዱ። እዚያም ሰይጣን እንዳይቀርብ በመስቀል አምሳያ ሐውልት አቆሙ። ከዚያ አልፈው በጽራዕ ምድር ሰፈሩና ከባሕሩ ዳር ውቅሮ የምትባል መቅደስ (= ቤተ ክርስቲያን) ሠሩ። ደግሞ መልኳ ያማረ ቀድመው ከተሠሩና ከተሰወሩ ከመቅደሶች (= ቤተ ክርስቲያኖች) ሁሉ የሚማሰላት የሌለ አንድ መቅደስ (= ቤተ ክርስቲያን) በመደቁ ሠሩ። በአጽሊ ምድር........” ይላል።

መጽሐፈ አክሱም የሚባለው መጽሐፍ ስለ አክሱሞች ይናገራል።

ሌላም ማስረጃ ለስጥህ:- እነዚህ የክርስትና ሃይማኖትና ቤተ መቅደሶችን በመላዋ ኢትዮጵያ ያስሰሩ ጥንታዊያን ነገሥታተ አክሱም ስለ አባ ሰላማ የተጻፈውን ልጥቀስ። አክሱም በማደጉ ግዕዝ በመማሩ አዲስ ኪደንን ከጽርዕ ወደ ግዕዝ የተረጐመው ከሳቴ ብርሃን (ሰላማ) ነገሥታቶቹ ወደ እስክንድርያ ልከውት ሄዶ የሥጋና የደሙን ሥርዓት አቀባበል፤ የቤተክረስትያናት ቀሳውስት ስርዓት....ወዘተ እንዲጠና እና መጥቶ እንዲያስተምር የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ በመሾሙ ደስ ብሏቸው ስሙንም “ከሳቴ ብርሃን” (ብርሃን አመንጣቂ/ገላጭ) ብለው ስም ቀጽለውለት በመላ ትግሬ የተሰማውን ዜና እንዲህ ይገልጸዋል””

<< ወሶ ሰምዑ አዝማደ እማሙ ዘሀገረ ግማድ፤ወሰምዑ፤ሰብዓ አይባ ወሰብዓ ትግሬ፤ወጽራዕ ወሰብዓ ገረዓልታ፤ወሰብዓ ሐረማት ወድንግላት መቅድመ ኩሉ ሴሞሙ ለ፯ቱ ደቂቅ ዘነበሩ ወስተ ደብተራ ከመ ይኩኑ ልዑካነ ወይትራድዕዎ በጊዜ ቅዳሴ ወቁርባን ወወሰደሙ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ወሰመዮ ለፊንሐሰ ተንስአ ክረስቶስ ወለዐሮን ስምዖን ወለአዛርያስ ማቴዎስ ወለአቤሜሌክ.........” እያለ ይቀጥላል።

እዚህ ላይ ልጠቅስ የምፈልገው ሁለት ነገሮች ነው። አንዱ ዋናው ክርክራችን ትግሬ ውስጥ “አማራ አንጂ ትግሬ የሚባል” በጥንት መጽሕፍትም ሆነ በመኖር (እንደ ሕዝብ) እንደማይታወቅ ተከታክረሃል። እዚህ ለማሳየት የፈለግኩት ትግሬዎች ከአባ ሰላማ ወይንም አብረሃ አና አጽብሐ በነበሩበት ጊዜ ጊዜ ጀምሮ እንኳን በአነስተኛ ማሳያ እንደማስረጃ እየነገረን ያለው በዘሀገረ ግማድ

*(ማለትም ከአክሱሞቹ አንዳንዶቹ ቀሳውስት አንደሚሉት እኔ ነግሴ በጀሮየ ከሰማሁት ሲናገሩ የንግሥት ማክዳ ልጅ የሆነው ከእስራሉ ሰለሞን ተወለደ የሚባልለት ቀዳማዊ ሜሌክ (አዛዥ፤ንጉሥ፤ዋና፤አለቃ) ከነ አዛርያስ፤ከነ ሳዶቅ...ባጠቃላይ “ሌዋውያን” የሚባሉት የእስራል ቀሳውስት “ጽላቱን” ይዘው ወደ አክሱም ከመጡት ተቆርጠው ግማሾቹ ወደ ዓይባ፤ ሓረማት፤ጽራዕ....አሁን ትግራይ ውስጥ (አንደርታ እና ውቅሮ አካባቢ የሚገኙትን ነገደ እስራሎች/ሌአውያንን/ ነው ዘሀገረ ግማድ ኢያለ ያለው)*

“..፤ወሰምዑ ሰብዓ አይባ፤ ወሰብዓ ትግሬ፤ወጽራዕ ወሰብዓ ገረዓልታ፤ወሰብዓ ሐረማት” ሲል የትግሬ ሰዎችም፤የገረዓልታ የጽራዕ ሰዎችም.... የሰላማን ዜናን ሰሙ ሲል በወቅቱ “ትግሬዎች” በቦታቸው እንደነበሩ እንጂ መጤ እንዳልነበሩ እና እንዲሁም “ወሰምዑ ሰብዓ ትግሬ እንጂ ወሰምዑ ሰብዓ አምሐራ አይልም”። ሆኖም አማራዎች የአክሱም ሰዎች አልነበሩም ማለት አይደለም። ምክንያቱም አክሱም “ትግሬን” ብቻ የሚያጠቃልል አይደለም፤ እስከ መላዋ ኢትዮጵያ እና ሶማሌ እንዲሁም አስከ ደቡባዊው ዓረብ ድረስ በቁጥጥሯ የነበረ አክሱማዊ ግዛት ስለነር ማለት ነው።

<u>እዚህ ላይ ሁላችሁም ልትገነዘቡ የምፈልገው ሌላው ነጥብ፤</u>

ትግሬ የሚለው ቃል የሚጻፈው በአማራዎች እንጂ በትግሬዎች አይደለም እኛ ትግራይ/ትግራዎት ነን ብለው የሚከራከሩ የዘመናችን አተላዎች፤ ካፍንጫቸው

የማይርቁ ደናቁርት ትግሬዎች አሉ። እነሱን ጀሮ ሳትሰጡ በዛው ብንሄድም፤ ጸሐፊዎቹ “አማራዎች” ናቸው ማለት ነው። ስለዚህ ከላይ የተመሰከረው የጥንት መጽሐፍ የተጻፈው በትግሬዎቹ ሳይሆን በአማራዎች ወይንም በግዕዝ ተናጋሪዎች ከሆነ ትግሬዎች መኖራቸውን ግልጽ ማሳያ ነው ማለት ነው። አማራዎች ናቸው የጻፉት ከተባለም፤ ትግራይ ውስጥ አማራዎች የነበሩበት ቦታ “ወሰምዑ ሰብዓ አምሐራ” ብለው ለምን አልመዘገቡም? ግን አንድ ነገር ልግልጽልህ የምፈልገው ጎጃም ውስጥ በሸዋ “ደብረ እለ፤ በጎጃምም “መርጦለ ማርያም” የታበሉ መቅደሶች ሰርተዋል። እነዚህም ሲመዘገቡ “ወኃለፉ እምህየ ወበጽሑ ምድረ ሐረማት ወሐነጹ በህየ አሐተ መቅደስ ዘትሰመይ ሐውዜን ወእንዘ ሀለው በህየ ሰብዓ ትግሬ ...........ሐነጹ በሸዋ ደብረ እለ.........እያለ ይጠቅስ አና ኝጃም ውስጥም ያሳነጽዋቸው የነ መርጦለ ማርያምንም ይጠቅሳል። እንግዲህ “ሸዋ” እያለ ሲጠቅስ “ትግሬ” እያለ ሲጠቅስ፤ ጎጃም እያለ ሲጠቅስ ምን ለማት አንደሆነ ግልጽ ነው። በዚህ መልክ “ሰብዓ ትግሬ” የሚለው ትግሬ ማለት በትግሬዎች አይጻፍም ከተባለ ጸሐፊዎቹ አማራዎች ወይንም ግዕዝ ተናጋሪዎች ናቸው ማለት ነው። ምክንያቱም ሲቆርሱ ላራስ አያሳንሱ ብለን የምንከራከር ከሆነ ጸሐፍቶቹ አማራዎች ከሆኑ ለምን አምሐራን በተቀሱት የትግሬ መንደሮች አልተጠቀሱም?

አውነትም ዕብዶቹ እራሳቸው አብደው እኔንም ጭምር ዕብደት ውስጥ ከተቱኝ እና የገዛ ወገኖቼን ልከራከር አስገደዱኝ። ይቅር በለኝ ጌታየ!! ግን የግድ አንተ ትግራይ ምንምህ አይደለችም ሲለኝ የግድ ለኔም እንደምትደርሰኝ መከራከር መብቴ ነው።

ሰዓሊ አምሳሉም ሆነ ሌሎቻችሁ በአምሳሉ ገ/ኪዳን ጀልባ የምትቀዝፉ ሁሉ ትግሬ የትግሬዎችም ጭምር በዓይነታ (በጥንታዊነት) የሚወለዱ መሆናቸው እና አብርሃ እና አጽብሐ የተባሉት መንትያ ወንድማማቾች ነገሥታት እንኳ በነበሩበት ወቅት በሓውዜን ውቅሮ፤ዐይባ (እነዚህ ሁሉ አውቃቸዋለሁ ትግራይ ውስጥ ናቸው።) በተዘዋወሩባቸው በነዚህ ቦታዎች ሁሉ የትግራይ ኗሪዎችን በያሉበት እየሰበሰቡ ሲያነጋግሩ እንደነበር ያመለክታል።
ስለዚህ ወንደም አምሳሉ “ንጉሣኖች አብርሃ እና አጽብሐ” በተዘዋወሩባቸው የትግራይ ቦታዎች ሁሉ “አማራዎች እየሰበሰቡ እንዲህ አሉ” የሚል ማስረጃ ካለህ ንገረን። ካሳየኸኝም የበለጠ የኔው “ሁለቱም ያንድ ዘር ግንድ ናቸው” የምለውን መከራከርያየ ታጠናክርልኛለህ ማለት ነው። ስለሆነም በዚህ ዕብደት እየሔድን ያንድ ቤተስብ ነገዶች አንዱ መጤ አንዱ የውጭ እየተደረገ የሚጋለበው የዕብዶች

መጋለብ፤ ሉዓም ቢደረግለት ለሰላሙ መልካም ነው። ያልተማሩ ሰዎች በእንዲህ ያለ ዕብደት ቢዋኙ አለማወቅ ስለሆነ ቢሰቀይምም እንደ ተማሩት ዓይነት የሚሰቀጥጥ አስቀያሚነት አይሆንም። መቸም ለነገሩ እንጂ ፤ንጹሕ ትግሬ፤ንጹሕ አማራ፤ንጹሕ አሮሞ፤ንጹሕ ሶማሌ፤ጉራጌ......የሚል ሰው ካለ ጠኔነቱ በሐኪም መመርመር አለበት። ነገድ ስሜት እንጂ ተጨባጭ አማራ፤ትግሬ፤አሮሞ፤ሶማሌ....የሚባል የደም ዓይነት እስካሁን ድረስ በምርመራ ሲረጋገጥ አይቼ አላውቅም። እንዲህ ማድረግም "ዕብደት" ነው።

<u>ስለጠቀስካቸው የአክሱም ነገሥታት ስም አማርኛ መሆኑን መልስ።</u>

አስቀድሜ እንደገለጽኩት ስም መሪ ሊሆን የሚችል ከሆነ ወልቃይት ያለው የትግሬ ስም በርካታ ቦታዎችም የትግሬ ነው የሚል ሙግት ያመንክ ትመስላለህ። ባጭሩ አንድ ንጉሥ ወይንም በየጊዜው የነገሥ ነገሥታት ሕዝብን አይወልዱም/አይወክሉም። እራሳቸው እና በዞርያቸው የሚገኙ ቤተሰባቻቸው እና በጋብቻ ሚጋቡዋቸው ቤሰቦች ብቻ ነው "ትውልዳቸው የሚውክሉትነና የሚቆጥሩት እንጂ መላውን ሕዝብ አንደ አዳም እና ሔዋን ሆነው ሕዝብን በነገዳቸው አይወክሉም"። አንተም አስቀድመህ እንደነገርከን የአክሱም ነገሥታት የአይሁዶች/የጽርዕ ስም፤የግሪክ ወዘተ....ስም የያዙ አሉ። እነዚህ ግን ለምን እንዲያ እንደተሰየሙ አንም ሆነ እኔ አናውቀውም። በስም የምንሔድ ከሆነም እንዲያ ከሆነ አክሱሞች ማለትም ባንተ አባባል "አማራዎች" (ትግሬዎች እዚህ አልተጨመሩም የሉም ስላልከ) ግሪኮች አይሁዶች ነበሩ ማለት ነው። ከሆኑም ትግሬ የግሪኮች፤የእስራሎች አገር ነበር ማለት ነው። ባጭሩ ግን ነገሥታቱ ከየትም ይምጡ ከየትም ፤መላውን የአካባቢውን ሕዝብ ነገድ ሊወክሉ ከቶ ፍጹም አይቻላቸውም። ያ ሊሆኑ አቅም ካላቸው ንገሥታት ሳይሆኑ፤ወደ አዳም እና ሔዋንንት ተቀይረው የአዳምና የሔዋን ቦታ ይዘው ያንን ሁሉ አሕዛብ በራሳቸው ነገድና፤ደም አጥንት ገንብተውት ነበር ማለት ነው።

የኔ ወንድም ነገሥታቱ ከጥንት እስከ ቀ/ሃይለስላሴ ያለውን የጋብቻ ትስስር ስትመለከት፤ እነሱን ከሚመስሉ እና ሳት ብሎም እነሱን የሚመስሉ ሥልጣን ተቀናቃኝ ነገዶች ይጋባሉ እንጂ መላውን ሕዝብ ነገድ የማራባት አቅምም ችሎታም የተሰጣቸው የፈጣሪ ጸጋም የለም። <u>ብዙ ተባዙ</u> የተባለው ትርጉም ከእልፍ ኣእላፍ የተለያዩ ነገዶች <u>እተጋባችሁ ተራቡ፤ሌሎች ነገዶችንም በስራችሁ ፍጠሩ...</u> ማለት እንጂ "አማራ ከሚባል፤ትግሬ ከሚባል፤ ኦሮሞ ከሚባል..ነገድ ከመጀመሪያ ዓለም

ሲፈጠር እስካሁን "ወጥ ሆኖ የተፈጠረ ነገድ፤ አሁንም ያለተቀየጠ፤ያልተዳቀለ ነገድ ነው ማለት አይደለም። ስለሆነም ጠባብ ትግሬዎም ሆናችሁ ጠባብ አማራዎች አደብ ግዙ! ይላችኋል ጌታቸው ረዳ።

አማርኛ የያዙ አክሱማዊያን የነገሥታት ስም ከጠቀስክ የትግርኛ ስም ያላቸው ነገሥታትም አሉ። እዛ ጊዜ አላባክንም፤ ምንም ማለት ግን አይደለም። ሌላ ቀርቶ ለአክሱም ጽዮን የተሰጣት ከ <u>124</u> በላይ ርስት ጉልት ብዙዎቹ በትግርኛ እና ግዕዝ ስም ያላቸው ገጠሮችን ልጥስና እንዲህ ከሆነ ለምን አማርኛ ያለው ርስት ጉልት ትግራይ ውስጥ ልናገኝ አልቻልንም የሚለውን ልጠይቅ።

አብርሃ እና አጽብሐ ለጽዮን የሰጣት ርሥት ጉልት ለምሳሌ ልጥቀስ፡
እድ አስሐትያ፤ሰላዕ፤ዓድ ብጽዓት፤ ዓዲ ገዛይ፤ ዓዲ ቅኔ፤ ዓጽሚ ሐርማዝ፤ ኰኰሒ፤ ዓዲ ገርጣጥ፡ዓዲ ደቂ ዳዊ፡ ዓዲ ምልዖ፤ ሐንከስቲ፤ማይ ብዋከ፤ዓድ ስየ፤ ድራ፤ ምላዞ፤ዝባን ዕገለ፤ዓዲ፤ንበረ ዕድ፤ማይ ምውት፤ ዓድ እታይ፤ዓድ መሠረት፤ዓድ ሥዩም፤ ዓድ ሓንከራ፤ማይ ዘግራ፤(ዘሬ ከጊዜ በኋላ እኔ በልጅነቴ ማይ ዛግራ ብለን እንጠራው ነበር)፤ ዓድ ራዛ፤ዓድ ጸሐፊ፤ ፍልፍሊ (በልጅነታችን ጌታችን ያረገበት ዕለት ለማክበር ስንሄድበት የነበረ ከአክሱም 5 ወይንም 8 ኪሎሜትር ርቀት የሚገኝ ዱራማ እና ለም ገጠር)፤ማይ ጸዓዳ፤ሰመማ፤ማይ ጣፋት፤ ዓድ ጽሕሎ፤ዓድ ሳሁ፤ ዓዲ ቐርኒ (ቀርኒ)፤ዓዲ ቀርቀራ፤ዓድ ዋጦት፤ምላዞ፤ዝባን ዕገለ፤ ክቱር፤ ማይ ጣፋት ወዘተ....ወዘተ......

የተባሉ በትግራይ በተለይ አክሱም እና ሽሬ፤ ዓድዋ እስከ ሁለት አውላዕሎ ውቅሮ ድረስ.....እንደርታ አካባቢ የሚገኙ ብዙዎቹ የተጠቀሱት ቦታዎች የጽዮን ርዕስ ጉልት ሆነው በነገሥታቱ በአብርሃ እና አጽብሐ የተሰጡ የማይነኩ ለጽላትዋ፤መገልገያ የሚውሉ ርስቶች ናቸው። እነዘሂህ ከመ 124 ርዕሰቶች ብዙዎቹ ተግርኛ እና

ሦስት የሚሆኑ አምርኛ መሰል ስም ያለቸው አግኝቼአለሁ። እነሱም በማጠጋጋት ዓድ ምክር፤ ጦማሎ፤ድምበዛ፤ሓመድ አልባ (አመድ አልባ) ናቸው።

ድምበዛ የሚል ስያሜ አንዳንዶቹ ተርጓሚዎች ደምበዛ ማለት ነው ይላሉ። ጦማሎ ደግሞ አማርኛ ነው ይላሉ። ጾሜአለሁ ለማት ይሆን? እንጃ፡፤ በዚህ ስም የሚታወቁት ዓድዋዎች ናቸው። ሐመድ አልባ ሲተረጎም በትግርኛው "ሐ" የጀመረው አማርኛው "አ" የሚጀምረው ነው "አመድ" <u>አልባ</u> የሚለው አማርኛ

ነው፤ "አልቦ" (በግዕዝና በትግርኛ ነው)። ስለሆነም አልባ የሚለው አማርኛ "የሌለው/ምንም" እንደማለት'አመድ የሌለው እንደማለት።
እንግዲህ ይህ ሁሉ ከዘረዘርን ብዙዎቹ የገጠሬው ስሞች ትግርኛ እና ግዕዝ ሆነው እናገኛቸዋለን። እነኚህ ስሞች ደግሞ ከጥንት ጀምሮ እነ አብርሃ አጽብሃ በነበሩበት ዘመን ጀምሮ የተሰየሙ ቦታዎች ናቸው። ስለሆነም ትግሬዎች የጥንቶቹ የትግሬ አክሱም ሰዎች ናቸው የምለውም ለዚህ ነው። እንደርታ ውስጥ በድሮ ዘመንለም ነበረች የሚባልላት "አጉላዕ" የምትባል ገጠር አለች።ከተማ ለማድረግ ምቹ ቦታ ነች። እኔ የማውቃት ትንሽ ገጠር እንዳለች ነው የማውቃት። ዛሬ ከትማለች ይባላል። አጼ ዮሐንስ ስሟን 'ጎንደር' ብለው ሊሰይሟት ሞክረው ነበር ሲሉ የታሪኽ ኢትዮጵያ ደራሲ ደብተራ ፍስሃ አብየዝጊ ጽፈውታል (ገጽ 18- ታሪኽ ኢትዮጵያ)። ዘሬ ጎንደር ተብላ ቢሆን ኖሮ ፤አማራዎች ያችን በጥሩ መካረከሪያ ይጠቀሙባት ነበር ማለት ነው። ለዚህ ነው ስም ብዙውን ጊዜ ሙሉ በሙሉ ፍንጭ ይሰጠን እንደ ሆነ እንጂ "ምንነት"ግን ሊሰጠን አይችልም የምለው።

ለማጠቃለል በትግራይ ውስጥ ሲነገሩ የነበሩ ሁለት ታላላቅ የሚባሉ ጽሐፈት ያላቸው ቋንቋዎች፤ ግዕዝ እና የከለው ሰዎች የሚናገሩት ትግርኛ ነው። የቀደምዎቹ አክሱማዊያን ሊቃውንት የሚናገርዋቸው የስርጽ እና እብራይስጥ' ቋንቋን ሳናወሳ መላት ነው።

<u>ባጭሩ ስለ አክሱም ለማወቅ የሚፈልጉ ትንሽ ልበል።</u>

አክሱም የተወለደ ሁሉ ርስት ፤ጉልት አለው ማለት አይደለም። የተወሰኑት ብቻ ናቸው። ርስትና ከጋብቻ የተገለሉ ከጥንት እስራል ጽላቱን ይዘው ከመጡት 12 ነገዶች (የሚባሉት) አብረው የመጡ የሚባልላቸው (እኔ የማልስማማበት ግን አከራካሪ የሆነ) አንጠረኞች፤ማሲንቆ መቺዎች (ዋጦት ይባላሉ በትግርኛ) ሃም የሚባሉ የሌዊ ልጆች (ካሕናት ናቸው) (ምሳሌም ሃም አገር የለው ሰማይ ምሰሶ የለው) ይባላል። ከነዚህ ሌሎች ለምሳሌ "መአሡሮ" የሚባሉ (እኔም በልጅነቴ እያቸው ነበር) ጽዮን/ጽላት/ለትዕይንት ስትወጣ ፊት ለፊት ጅራፍ እያስጮኹ ከታቦቷ ፊት ለፊት እየመሩ የሚሄዱ ነገዶችም ርሽት የላቸውም። ከጋብቻም የተገለሉ ናቸው። (27) አክሱም ማለት በዓረብኛ ትርጉም 'የምኄት ቦታ፤የገነት ቦታ" ማለት ነው ይላሉ።ደብተራ ፍስሃ ሲገልጹ "የትግሬ ሰዎች ስም ስያወጡ ወይ ወደ ግዕዝ ወይንም ወደ አማርኛ ይሮጣሉ። ኤጼ ዮሐንስ ማይ ዓዓ (ዓድዋ ውስጥ) ቤት ካስሩ በኋላ ቦታው ከፍተኛ እና ሁሉንም አካባቢ በግልጽ የሚያሳይ ከፍታ ስለነበረው ምንም አንኳ በአመርኛ ቢጽፉም በአማርኛ መናገር የማይፈልጉ ቢኖሩም እንኳ "የት ነበርሽ" አልዋት። ከዚያ ዘመን ጅመሮ እስካሁን ድረስ "የት ነበርሽ" ተብላ ቀረጭ። (28) ይላሉ። ብዙዎች የአክሱም ነገሥአት ከኪለው ስሞች

ውጪ የአርብኛ ስም አላቸው። ለምሳሌ አረቦች ካሌብን “ኢላ አጽባኣን” ብለው ይጠርዋቸዋል። ይህም ናግራን በታበለው ዓረብ የዛሬው ዓረብ ምድር ጦር ገጥሞ ስላሸነፋቸው በግዕዝ ጸብኣ በትግርኛ “ተጻባኢ” ተቃራኒ ማለት ሲሆን በግዕዝና ዓረብ ግን “አሸነፈ” ማለት ሲሆን የግብር ስም እንጂ የመጠሪያ ስም አይደለም። (35)

<u>በመጨረሻ ሰዓሊ አምሳሉ፤-</u>

ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ ትርጉም ስትሰጥ ምኒልክ ማለት “ምን ይልክ” ማለት ነው ብለሃል። ትርጉም የመስጠት መብትህ የተጠበቀ ቢሆንም። ምኒልክ መነሻ ስሙ የተገኘው የሰለሞን ልጅ የሆነው አማርኛ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ስም ነው። ሁለት ስሞች ነበሩት። “እበነ ሐኪም እና “<u>እብን</u> መሊክ” ታዲያ በኋላ “ተጎርዶ” ምኒልክ ተባለ። ትርጉሙም “እበነ ሐኪም” (የገዢ ልጅ) ሲሆን “እብን መሊክ” (የንጉሥ ልጅ) ማለት ነው። እብን የሚለው ዓረባዊ ቋንቋ ከፊት ተጨምሮበታል። ወደ ግዕዝም “<u>ኣብ</u> መሊክ” ይባላል (25)፡ ይኼውም “ቀዳማዊ ምኒልክ” ማለት ነው። አንተ ምን ይልክ/ ምን እልክ/ ብሎ የመተረጎሙ ግን መብትህ ነው።በመጨረሻ አንድ የቅርብ ወዳጄ የሆኑ ኢትዮጵያዊ ምሑር አማራና ትግሬ አንድ ዘር ናቸው። የሕዝብ ቈጠራ ሲጀመርም በአንድነት ነበር የተቈጠሩት።ሲሉ ነግረውኛል፤ በዚህ ትረካለህ አትረካም ያንተ ፋንታ ነው። እያልኩ ለዛሬው ግን ሰዓሊ ሆይ፤ ወያኔዎች ስትፈልጉ ውልቅ በሉ ማለት ትችል እንደሆን እንጂ “ትግሬዎች” ከትግሬ መሬት ውልቅ በሉ እና እኛ <u>አማራዎች እንግባበት</u> የሚለው ስዕልህን ወደ ተገቢው ስዕል እንድታስተካክልበት ይረዳህ ከሆነ ይኼው ምክሬን ለግሻለሁ ። ያንድ ዘር ግንድ ወንድም እህትማማቾች ነን እና ካልተከባበርን ሕዝባችን ወደ ባሰ ጦርነት ከትትን ለጠላት ምቹ መንገድ እንዳንከፍትለት ተከባብረን በሰላም እንኑር። አመሰግናለሁ። ላስተያየታችሁ በሚከተለው ኢመይል ብትልኩ መቀበል ዝግጁ ነኝ። ይህ ጽሑፍ ማንም ሰው በድረገጾቹ መለጠፍ እና መነጋገርያ እንዲሆን ፈቅጃለሁ።ወንድማችሁ

ጌታቸው ረዳ (ዘብሔረ አክሱም) ኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ
getachre@aol.com